

# መጥምቁ ዮሐንስ

- የኢየሱስ እናት ማርያም የዮሐንስ እናት የኤልሳቤጥ ዘመዷ. መልአክ ለማርያም ተገልጦላት ኢየሱስን እንደምትወልድ ከነገራት በኋላ ኤልሳቤጥን ለመጎብኘት ሄደች። እናም ኤልሳቤጥም ልጅ ለመውለድ ዝግጅት ላይ መሆኗን ተገነዘበች። ኤልሳቤጥና ባለቤቷ በእድሜ የገፉ ሰዎች ስለነበር የሚወልዱት ልጃቸውም ልዩ ልጅ ነበር። እግዚአብሔር ለልዩ ተልእኮ የመረጠው ልጅ ነበር። ተልእኮውም የሰዎችን ልብ ለሚመጣው መሲህ ማዘጋጀት ነበር።

- ነቢዩ ኢሳያስ ስለእርሱ "በምድረ በዳ ሰዎች ራሳቸውን ለሚመጣው ኢየሱስ እንዲያዘጋጁ የሚጣራ ድምፅ" በማለት ተንብዮ ነበር። በእርግጥ ዮሐንስ ስለኢየሱስ ሲናገር ኢየሱስ ከእርሱ እንደሚበልጥና የእርሱን የእግሩን ጫማ እንኳን ለመያዝ ብቁ እንዳልሆነ በዙሪያው ለነበሩ ሰዎች ይናገር ነበር።

- ዮሐንስ ልብሱ ከግመል ፀጉር የተሰራ ሲሆን በወገቡ ዙሪያም የቆዳ ቀበቶ ይታጠቅ ነበር። የሚኖረው በበረሃ ሲሆን ምግቡም የዱር ማርና አንበጣ ነበር።

- በዮርዳኖስ ዙሪያ በሚገኙ መንደሮች እየዞረም ሰዎች ንስሐ እንዲገቡና የኃጢአት ይቅርታ እንዲቀበሉ ይሰብክ ነበር። ብዙ ሕዝብ ወደ ዮሐንስ እየመጡ ኃጢአታቸውን እየተናዘዙ በዮርዳኖስ ወንዝ ይጠመቁ ነበር።

- ዮሐንስም ከዚህ በኋላ የፅድቅ ኑሮ እንዲኖሩ ይነግራቸው ነበር። እነርሱም ምን ማድረግ እንዳለባቸው ይጠየቁት ነበር።
  እርሱም ሁለት ልብስ ያለው አንደኛውን ምንም ልብስ ለሌለው እንዲያካፍል ነገራቸው። በተመሳሳይም በቂ ምግብ ያላቸው ምንም ለሌለው እንዲያከፍሉ ነገራቸው።

- ግብር ሰብሳቢዎችም ምን ማድረግ እንዳለባቸው ጠየቁት። እርሱም ታማኞች እንዲሆኑና መሰብሰብ ከሚገባቸው በላይ ጨምረው ግብር መሰብሰብ እንደሌለባቸው ነገራቸው።

- እንዲሁም ወታደሮችን ጉቦ እንዳይወስዱና በሐሰት ሰዎችን እንዳይወነጅሉ ነገራቸው። በሚያገኙት ገቢ ደስተኞች እንዲሆኑና እንዳያጉረመርሙ መከራቸው።

- ዮሐንስ ሰዎችን ባያስደስታቸውም እንኳን ሁልጊዜ እውነትን ይናገር ነበር። ንጉስ ሔሮድስን እንኳን ሳይቀር በሰራው ክፉ ስራ ምክንያት ፊት ለፊት ተቃውሞታል። ይህ ተቃውሞውም ለሞት አብቅቶታል።

*ይህ የመጥምቁ ዮሐንስ ታሪክ የሚገኘው በሉቃስ ወንጌል በምዕራፍ 3 ውስጥ ነው።*

http://gardenofpraise.com